# ***እንደ ስሙ ብቅ ብሎ የጠፋው ቀስተዳመና እና ሌሎች የፕሮፌሰር ብርሁኑ ነጋ ፓርቲዎች ለምን ለድል አልበቁም???***

በፍስሀ ገመዳ 12-22-16

ከአዲስ አበባ

የአገራችን የፓለቲካ ታሪክ ውስብስብ እና ብዙ ታሪኮች የተሰሩበት እና አሁንም የተለያዩ ታሪኮች እየተሰሩበት የሚገኝ ከመሆኑ አንፃር ብዙ ሰው እራሱ ከተሳተፈበት፣ ከሰማው፣ ካነበበው እና በአይኑ ካየው በመነሳት ብዙ የተፃፈበት እና እየተፀፈበት መሆኑ ሁሉም ግልፅ ነው በመሆኑም እኔም ከማየውና ከማነበው በመነሳት ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ በሀገራችን ፖለቲካ ስማቸው በጉልህ ከሚነሱ የፓለቲካ መሪዎች አንዱ የሆኑትን ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ ከወጣትነታቸው ጀምረው የተሳቱፉባቸውና የመሰረቱዋቸው ድርጅቶች በሀገራችን ፓለቲካ ለድል ለምን አልበቁም/ አይበቁም የሚለውን ያስተዋልኩዋቸውን ለማካፈል በመወሰን ይህችን አጭር ጽሁፍ አቅርቢያለሁ፡፡

## 1. <u>ፕሮፌሰር ብርሀኑ ነጋ በኢህአፓ</u>

ፕሮሰፈር ብርሃኑ ነጋ በወጣትነት እድሜአቸው በኢህአፓ አባል በመሆን ፓርቲው ደርግን ለመጣል የትጥቅ ትግል ለማካሄድ በመወሰኑ ከቆራጦቹ ወጣቶች ጋር በመሆን ወደ በለሳ ጎንደር የሄዱ ቢሆንም ትግሉ በጣም ፈታኝ እና አስቸጋሪ መሆኑን እንዲሁም አመራሩ በስልጣን ሽኩቻ ውስጥ መግባቱን ሲረዱ ከመሰል ጉዋደኞቻቸው ጋር በመሆን ትግሉን ጥለው በሱዳን በኩል ወደ አሜሪካ ፈረጠጡ ፡፡ ነገር ግን በኢህአፓ ውስጥ ከነበሩ ወጣቶች ውስጥ በጣም ጥቂቶቹ (37 ወጣቶች) ፣ጥቂቶች ቆራጦች ያልተንበረከክነው ነገ እልፍ እንሆናለን ታሪክ ምስክር ነው የሚል መፎክር ይዘው የኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ኢህዴን/ መስርተው የትጥቅ ትግሉን በማቀጣጠል እና ከሕወሀት ጋር ግንባር (ኢህአዴግ) በመፍጠር ከአስራ ሰባት መራራ የትግል አመታት በኃላ ደርግን ፈረካክሰው (ደምስሰው) ግማሹ ወደ ዙምባቤ ግማሹ ብርሀኑ ወደሚኖሩበት አሜሪካ እንዲፈረጥጡ ስላደረጉ እና ብርሀኑም ምንም እንክዋን በረሀ ከድተዋቸው ቢሄዱም አሜሪካ ሄደው

በመግራቸው እና እነዛ በረሃ የተውዋቸው ጀግኖች ስላልተማሩ ስልጣን ይሰጡኛል በሚል ተስፋ ወደ አገራቸው ተመለሱ፡፡ በመሆኑም ተምረው ሀገራቸውን ለማገልገል ከአሜሪካ የመጡ መስለው በመቅረባቸው ከትልልቆቹ የኢ.ህአዴግ መሪዎች ጋር ያለገደብ መገናኘት ጀመሩ (መለስ ዜናዊ፣ ታምራት ላይኔ፣ በረከት ስምኦን እማ ጉደኛቸው ነበሩ ይባላል)፡፡ ነገር ግን ብርሀኑ ቢያዩ ቢያዩ ስለጣን ሊያገኙ ባለመቻላቸው ሌላ ስልጣን ሊያገኙ የሚችሉበትን መንገድ መጥረግ ጀመሩ፡፡ በመሆኑም የመንግስት ስልጣን ባያገኙም የኢኮኖሚስቶች ማህበር /መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት /NGO/ ከመሰሎቻቸው ጋር በመሆን መሰረቱ፡፡ በመሆኑም በዚህ ማህበር አማካኝነት አገራችን ኢትዮጵያ ከተለያዩ የተባበሩት መንግስታትና የአለም ባንክ ተቋማት እና አገራት የሚሰጣትን ድጋፍ በማማከር ስም ከፍተኛ ገንዘብ ሰበሰቡ (እንግዲህ ሰሜን ሆቴልና ጉሎባል ሆቴሎች የሚባሉ አለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ ሆቴሎችን ከበቤተሰቦቻቸው ጋር በሽርክና እንዳስገነቡ ይነገርላቸዋል፡፡ የሳቸው ድርሻ ስንት እንደሆነ እራሳቸው አንድ ቀን ይነግሩናል ወይም መንግስት እንደ እንግሊዛዊው የነፃነት ታጋይ አንዳርጋቸው ፅጌ ንብረት ወርሶ በዜና ይነግረን ይሆናል፡፡ ማንም እንዲያውቀው የሚያስፈልገው ግን እኝህ ሰው በአንድ በኩል በማማከር ስም የሀገሪቱን ከፍተኛ ሀብት እየዘረፉ በሌላ በኩል ደግሞ ለማስመሰል እና ለሀገር አሳቢ ለመምስል አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ይከፍላቸው የነበረውን ሶስት ሺ ብር የማትሞላ ብር አልወስድም ለችግረኛ ተማሪዎች ስጥዋቸው ይሉ እንደነበር ይነገራል፡፡ እንግዲህ በዚህ መልኩ ሀብት መከማቸት ሲጀምር አመራሩንም በማማከር ስም እንደፈለጉ ማግኘት ሲጀምሩ፣ አመራሩን መናቅ እኔስ ለምን የአገር መሪ አልሆንም የሚል ቅዠት ውስጥ ገቡ፡፡ ስለሆነም ከፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም ጋር በመሆን ቀስተ ደመና የሚል ፓርቲ አቁዋቁመው የቅንጅት አባል ሆኑ፡፡

## 2. ፕሮፌሰር ብርሀኑ በቀስተ ዳመና

ቀስተ ዳመና ፓርቲ ከፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም ጋር በመሆን ፕሮፌሰር ብርሀኑ የመሰረቱት ፓርቲ ሲሆን ምንም አባላት ሳይኖሩት የሁለቱም ፕሮፌሰርነት እና ምላስ ብቻ በመያዝ የተለያዩ ጠንካራ ፓርቲዎች የተሰባሰቡበትን ቅንጅት ተቀላቀሉ፡፡ እንግዲህ ይታያቹህ ስም ባልጠፋ ቀስተ ደመና እናም እንደስሙ ብቅ ብሎ እልም ያለው ማለት ነው፡፡ ሁላችንም እንደምናውቀው በ1997 ቅንጅት በውሸትም በማሳመን ብልጫም ኢ.ህአዴግን በልጦ በብዙ ቦታ በተለይም በከተሞች ላይ በአብላጫ ድምፅ አሸነፈ እናም እነ ልደቱ አያሌው፣ ሀይሉ ሻወል እና ሌሎችም ለበርካታ አመታት ገንዘባቸውና ጉልበታቸውን

መስዋእት አድርገው ያመጡትን ድል ብርሀኑ ነጋ ውሸማቸው እንደሆነች የሚነገርላትን ወ/ሮ አና ጎሜዝ በወቅቱ የአውሮፓ ህብረት ተወካይ ታዛቢ የነበረች በመተማመን እና በሴትየዋ እና አንዳንድ በአሜሪካ የሚኖሩ የደርግና የአፄው ቅሪቶች አይዞህ ባይነት ዋናዎቹን የቅንጅት መሪዎችን እንደልማዳቸው በመካድ እና ወደጎን በማግለል ቅንጅትን ወክለው ስለስልጣን ክፍፍል ከኢህአዴግ ጋር ድርድር ማካሄድ ጀመሩ ይሄኔ በብርሃኑ ስራ ያልተደሰቱት እነ ልደቱ፤ የወቅቱ የቅንጅት መሪ ሀይሉ ሻወል እና  በሌሎቹም አባላት ውስጥ ቅሬታ በመፈጠሩ ድሮም ምንም መሰረት ያልነበረው ቅንጅት በብርሀኑ ቅጥ ያጣ የስልጣን ፍላጎት ምክንያት ድንብርብሩ ወጣ ፡፡ በወቅቱ ያወጡዋቸው የነበሩ መግለጫዎች እርስ በርስ የሚጣረሱ እና እጅግ አደገኛ እየሆኑ መጡ፡፡ ለምሳሌ በቲያትርና ድራማ ስራዎቹ ተወዳጅ የነበረው ደበበ እሸቱ ሳይቀር እነዚህን ሰዎች አግልሉ ከእነሱ ጋር ቡና እንዳትጠጡ፤ ለቅሶ እንዳትሄዱ የመሳሰሉት ማህበራዊ ጉዳዮች ከነዚህ የኢህአዴግ ደጋፊዎች በተለይ የትግራይ ሰዎች ጋር እንዳትፈፅሙ ይህን ቢራ እና ለስለሳ መጠጥ እንዳትጠጡ አግሉሉ በተከታታይ ለምንሰጣችሁም መመሪያ ተከታተሉና ፈፅሙ ብለው አወጁ፡፡ በተቃራኒ ወገን የተሰለፈውም ሀይል ይህንንማ ዝም ብለን አናይም በርዋንዳ ስንሰማው የነበረውን ጉድ አገራችን በምንም ተአምር እንዲደገም አንፈቅድም በማለት መንግስት የማያዳግምና የሚመጥናቸውን እርምጃ እንዲወስድ መጠየቅ ጀመረ፡፡ መንግሰትም ለቅንጅቶች ፉከራና ቀረርቶ የሚመጥን እርምጃ መውሰድ ሲጀምር ድሮም የነ ተሎ ተሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ ነበርና  መቀናጀት የማይገባቸው የተለያዩ ሀይሎች የተቀናጁበት ቅንጅት ምንም እን⑧ መሪዎቹ እነ ብርሀኑ ነጋ ሲናገሩ ሰማይ የሚያፈርሱ ይመስሉ የነበረ ቢሆንም ትንሽ እን⑧ ሳያንገራግሩ እንደ እምባይ ካብ ፍርስርሳቸው ወጣ ላይመለስ ቅንጅትም እንደ አባታቶቹ ደርግና የአፄው መንግስት ታሪክ ሆነ፡፡ በመሆኑም ቅንጅትም ላይመለስ እንደ ደርግ ተበታተነ ፡፡ ደርግም የተፈረካከሰው ህዝብን እንደህዝብ ማጥላላትና ለማጥፋት በመነሳቱ ስለነበር ነው እና ቅንጅትም ከነዚህ ጋር ቡና እንዳትጠጡ፤ አግልሉዋቸው ማለት ሲጀምሩ ተፈረካከሱ ምክንያቱም የህዝብ ፍቅር እና አንድነት ለማፈራረስ በመጀመራቸው ፈራረሱ፡፡ ይህ ሁሉ የሆነው በእነ ብርሀኑ ነጋ መረን ያጣ የስልጣን ፍላጎት ምክንያት ሲሆን በወቅቱ የቅንጅት አመራር የነበሩ አብዛኛዎቹ ለእስር ተዳረጉ፡፡

እነ ብርሀኑም በሰፈሩት ቁና ሊሰፈሩ ወደ ቃሊቲ ወረዱ ፤ ያ! ሁሉ ፉከራና ቀረርቶ የተወሰነ የድሀ ልጅ ሂወት ቀጥፎና እነ ብርሁነን ደግሞ ወደ ቃሊቲ ወስዶ በረደ፡፡

ከተወሰነ አመታት እስራት በኃላ የሀገራችን ታዋቂ ሽማግሎች እነ ሀይለ ገብረስላሴ፤ ፕሮፌር ይስሀቅ ኤፍሬም እና ሌሎችም ሽምግልና ገብተው መንግስትን በማሳመን ከእስርቤት እንዲፈቱ ተደረገ፡፡ ነገር ግን ቅንጅት እንደ ቅንጅት መቀጠል አልቻለም ሆኖም የቅንጅት አባል ድርጅቶች ተዳክመውም ቢሆን በተናጠል ህልውናቸው ቀጥለዋል ቢሆንም የብርሀኑ ቀስተ ደመና ግን እንደስሙ ብቅ ብሎ ጠፋ ፡፡ ድሮስ ስም ባልጠፋ ቀስተዳመና ብሎ ስም እንዴት ይዘልቃል ስም ይመርህዎ ለተግባር አይደለም ነገሩ፡፡ ቀስተ ዳመና ደግሞ ብቅ ብሎ የሚጠፋ እንጂ በቋዋሚነት የሚታይ አይደለም፡፡

አሁን ደግሞ እነ ብርሀኑ ያስጠነቆሉ ይመስላሉ ፤ወያኔም ከሻእብያ ጋር በማበር ነው ለድል የበቃችው ብሎው ነው መሰለኝ የትጥቅ ትግል በወጣትነታቸው ያልቻሉትን በስተእርጅና ሊሞክሩት በሰሜን በኩል ግንቦት ሰባት የሚባል ድርጅት መስርተው እየተንቀሳቀስን ነው እያሉን ነው፡፡

## 3. ፕሮፌሰር ብርሀኑ በግንቦት ሰባት

እንግዲህ ይታይቸሁ አሁንም ስም ባልጠፋ ግንቦት ሰባት፤ እንግዲህ በ1997 ዓ. ም የተካሄደው ምርጫ የተካሄደው በግንቦት ሰባት ቀን ነበር ይህ ምርጫ ቅንጅቶች አሸንፈንበታል ብለው የሚያምኑበት ሲሆን እላይ እንደገለፅኩት ባልሆነ መንገድ ለመሄድ በመሞከራቸው ለእስር የተዳረጉበት እና በርካታ የድሀ ልጆች የለቁበት ክስተት ሁኖ አልፈዋል፡፡ ነገር ግን ብርሀኑ ከእስር ተፈትተው ወደ አውሮፓ እና አሜሪካ ሄደው ለደጋፊዎቻቸው ንግግር በሚያደርጉበት ወቅት ጭብጨባ ሲበዛ ያቁዋቁዋሙት ድርጅት ሲሆን ስያሜውም የግንቦት ሰባት 1997 ዓ.ም ምርጫ መታሰቢያ ነው፡፡
እንግህ የትጥቅ ትግል መድረክ ላይ እንደ ማውራት ቀላል አይደለም ብዙ ጉልበት የሚጠይቅ፤ የአመራሩ ግንባር ቀደም አመራር እና እርአያነት የሚጠይቅ እንጂ በተልእኮ መርቶ ለድል ማብቃት እንደማይቻል ከአንጋፋውና ከርታታው ድርጅት ኦነግ መማር ይቻል፡፡ ለማኝኛውም መድረክ ላይ ማውራት መውረስ ይቻላል የበለጠ አሳምሮም መናገር ይቻል ይሆናል፡፡ የትጥቅ ትግል ማካሄድ፤ ጀግንነትና ቁርጠኝነት የሚወረስ አይመስለኝም፡፡ በመሆኑም ፕሮፌሰሩ አሜሪካም ሆነ አውሮፓ እንዲሁም ኤርትራ ሄደው ቢያቅራሩ ለውጥ አላመጡም በተደጋጋሚ የጦርነቱ ፍሽካ ነፍተናል፤በሁሉም ቦታ አለን

እየገሰገስን ነው ቢሉም ጦርነትን በእጅጉ የሚያውቀው የኢትዮጵያ ህዝብ ማሳመን ቀላል አይሆንም ምክንቱም ጦርነት ካለ ቦታ መቆጣጠር እና መልቀቅ ስላለ እነ ብርሀኑ የያዙትም ሆነ ያስለቀቁት ቦታ የለም፡፡ በእርግጥ ፕሮፌሰሩ ድሮም ቢሆን ቱሪናፋ ስለሆኑ ፍሽካው ተነፋ ይባል እንጂ ጨዋታ የለም ምክንያቱም ጨዋታው ጀግንነትና እውቀት ይጠይቃል ወታደራዊ እውቀት ማለቴ ነው በመጮህ ቢሆን የሚያክላቸው ያለ አይመስለኝም፡፡

ጀግንንነት ግን በልጅነት ያልነበራቸውን አሁን በእስተእርጅና ከየትም ሊያመጡት እንደማይችሉ ቢታወቅም አሁን በወዳጆቻቸወና በእንጀራ አጋሮቻቸው በኩል በረጋ ወጡ፤ ፍሽካ  ነፉ ተብሎ ነበር ግን ተጫዋች ስላጡ ወይም እንደለመዱት ጉዋደኞቻቸውን በርሀ ላይ ጥለው/ ከድተው አሜሪካ ገብተዋል፡፡ ድሮስ በልጅነት የሌለ ጀግንነትና ቆራጥነት አሁን ከየት ይመጣል፡፡

ስለሆነም ግንቦት ሰባትም እንደስሙ የግንቦት ሰባት 1997 ዓ.ም መታሰቢያ ሁኖ መቅረቱ አይቀርም፡፡ ይህም እንግዲህ ሌላኛው ስም ይመርህዎ ለተግባር ማሳያ ነው፡፡

ለማጠቃል ፕሮፌሰሩ እንግዲህ ከወጣትነታቸው ጅምሮ በተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች የተሳተፉባቸውና የመሰረትዋቸው ድርጅቶች እንዳሉ ቢታወቅም እስከአሁን ድረስ አንድኑንም ለውጤት ያለመብቃታቸው ችግር ምን እንደሆነ እሳቸውና አማካሪዎቻቸው ኢህአዴግ እንደሚያደርገው ግምገማ ቢያደርጉና ራሳቸውን ቢፈትሹ የሚሻል ነው ብየ ባምንም ሀሳቡን እስካመጣሁት ድረስ ግን የራሴን ሀሳብ መግለፅ ግድ ስለሚለኝ ለመግለፅ ያህል ሰውየው ሞገደኛ፤ነገሮችን በትእግስት መገምገም ሳይሆን በስሜት መነዳት የሚወዱ በመሆናቸው እና ሌሎች በስንት ድካም ጥሩ ደረጃ ያደረሱትን የፓለቲካ ትግል እሳቸው ይጉቡና ትረምስምሱን ያወጡታል እናም ተሰናክሎ ይቀራል ብየ አምናለሁ፡፡ ይህንንም በተደጋጋሚ አብረዋቸው በሰሩ ፓለቲከኞች የተነገረ ነው፡፡ በተረፈ ግን ከዚህ በፊት የባህታውያን ድርጅት ምንጊዜም ቢሆን በሆታና በሞቅታ የሚመሩ ድርጅቶችን ያሸንፋል ብየ የፃፍኩትን ብታነቡልኝ ደግሞ የበለጠ ትረዱኛላችሁ፡፡

አመሰግናለሁ!!!!!!!

ኢትዮዮጵያችን ለዘለአለም ትኑር!!